# ሻ'ቢያን በእንኮኮ ወያኔን በአንቀልባ እሰከመቼ ?!

አሥራደው (ከፈረንሳይ)

**መንደርደሪያ:**

- « ዓይኔን ሰው አማረው፤
  የሰው ያለህ የሰው፤
  ሰው እፈልጋለሁ የሰው የሆነ ሰው፤
  ለአገር ተቆርቋሪ ልፈልግ ላምሰው፤
  .....................
  አገሬ ተባብራ ካልረገጠች እርካብ፤
  ነገራችን ሁሉ: የዕንቧይ ካብ የዕንቧይ ካብ » ::
  ቀኛ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሤ

- « ሲሰርቀኝ ያየሁት ቢጨምርልኝ አላምነውም »

- *« Seule la vérité blesse »*
« የምታቆሰል ብትኖር እውነት ብቻ ናት »

- *« Lorsque un seul homme rêve, ce n'est qu'un rêve. Mais si beaucoup d'hommes rêvent ensemble, c'est le début d'une réalité.»*

« አንድ ሰው ብቻውን ሕልም ሲያልም ህልሙ ህልም እንደሆነ ይቀራል፤ ነገር ግን ብዙ ሰዎች በአንድላይ ሆነው ሲያልሙ ሕልሙ እውን መሆን ይጀምራል»::

**መግቢያ:**

የአንድ አገር ትልቁ ሃብቷ ዜጎቿ ሲሆኑ፤ በተለይ ተሰፋ የሰነቀ፤ ጤናው የተጠበቀ፤ በራሱ የሚተማመን፤ በአገሩና በታሪኩ የሚኮራ፤ በትምህርት፤ በሳይንስና ቴክኖሎጂ የታነጸ፤ ከአይምሮው ጓዳ የሚፈልቁ ሃሳቦችን በተግባር ለመተርጎም ያልተገደበ፤ ለመናገርና ለመጻፍ ያልተለጎመ፤ ለግል ጥቅሙ ብቻ ሳይሆን ለወገኑና ላገሩ ጥቅም የቆመ፤ እራሱን አስከብሮ ሌሎችን የሚያከብር፤ ለአገሩና ለድንበሩ ቀናኢ የሆነ፤ አንድነት፤ ወንድማማችነት፤ ዕድገትና እኩልነትን መርሁ ያደረገ፤ ችግርና መከራን ሳይሆን መፍትሔን አፍላቂ ትውልድ ወሳኝ ነው::

በአንጻሩ የሻ'ቢያና የወያኔ እቅድ፤ ዜጎችን እርግፍ አድርገው በመጣል፤ የኢትዮጵያን ሃብት ብቻ በጋራ ቦጥቡጠው፤ ኤርትራ አፍሪካዊት ሴንጋፑር፤ ትግራይ አፍሪካዊት ሻንጋይ፤ እስኪሆኑ የራስን እድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል፤ የሚለው ደባቸውን በሕገ መንግሥት ተብዬው ውስጥ ሸጉረው፤ ምጽዋን ለኤርትራ፤ አሰብን ለትርራይ፤

*በባህር በርነት መድበው፤ ከጎንደርና ከወሎ ለም መሬት ነጥቀው፤ የምዕራቡን ድንበራችንን ለሱዳን ውለታና የወደፊት መያዣ እንዲሆን አስረክበው፤ ኢትዮጵያን በዘር፤ በጎሳና በሃይማኖት ከፋፍለው ዘወትር ጦርነት፤ ረሃብና ኋላ ቀርነት ሰፍኖ ሲተራመሱ እኛ ለመቶ አመት ሰላም እናገኛለን ብለው ከተሰማሙ ቆይተዋል ::*

*ዓላማው ይህ በመሆኑ ነው ወያኔ ከ20 አመታት የዘረኝነት አገዛዙ በኋላም እንኳን የነፃነት ቀንዲል በሆነች አገር ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ፤ ዛሬም የትግራይ ነጻ አውጪ ድርጅት ነኝ የሚለን::*

*ነጻ ከሚወጣው ሕዝብ ይልቅ የነጻ አውጪው ቁጥር በበዛባት አገራችን ኢትዮጵያ : ሠላም አንድነት፤ ዕድገትና ፍቅር እንዲሰፍን አይፈለግም: ይልቁንም ሕዝቡን በማዋከብ፤ በማባላትና በኑሮ ውድነት በማስራብ፤ በዕለት ተዕለት ኑሮው ተወጥሮ: ስለአገሩ እንዳያስብ በማድረግ፤ እርስ በርሱ እየተፈራራ እንዳይነጋገርና እንዳይጠያየቅ በወሬ ለቃሚ ካድሬዎች አስጠርንፈው፤ ተደራጅቶ እንዳይታገላቸው በማድረግ፤ በገዛ አገሩ የሁለተኛ ዜግነት እጣ አከናንበውታል ::*

*ወያኔ እራሱ የማያከብረውን ሕግ አውጥቶ፤ ሕግ በሌለበት አገር ሕግ አክብሩ እያለ « የምለውን እንጂ የምሠራውን አትዩ » በማለት፤ የወርቅና የማዕድን ዝርፊያውን፤ አሸባሪ እያለ ዜጎችን ከህግ በላይ በመሆን ማሰሩን፤ አርሶ አደሮችን ከቀያቸው ማፈናቀሉን፤ የሃብት ቡጥቦጣውን፤ ስርቆትና ንቅዘቱን (ሙስናውን) ቀጥሎበታል ::*

*ጥቂት ተቃዋሚ ነን ባይ የፖለቲካ ድርጅቶች ደግሞ በትንንሽ ጣቶቻቸው ስር ተደብቀው ሠላም በሌለበት፤ ሠላማዊ ትግል እያሉ፤ የገዛ አባሎቻቸውን እንኳን ከወያኔ ሰለባነት ሊታደጉ ባልቻሉበት ሁኔታ ውስጥ ሆነው፤ « የአህያ ባል ከጅብ አያሳጥልም » እንዲሉ በሚቀጥለው ምርጫ ወያኔን አጅበው አንድ የነበረችውን መቀመጫ ሁለት እንድትሆን (ያውም የወያኔ መልካም ፈቃድ ከሆነ) ለማድረግ፤ ሽር ጉድ ይላሉ (ይሽቀዳደማሉ)::*

*የሚገርመው ሕገ መንግሥቱ ይፈቅዳል የሚባለውን የመሰብሰብ፤ የመደራጀት፤ ሠላማዊ ሰልፍ የማድረግና የሥራ ማቆም አድማ : ማድረግ በማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ ሆነው እያለ : ስለ ሠላማዊ ትግል ሊሰብኩን ይሻሉ :: ሠላምን ማን ይጠላል ! ነገርግን፤*

- *ሕዝባችን : በወያኔ ደህንነትና ካድሬዎች ተቀፍድዶ ተይዞ አሸባሪ እየተባለ ትንፍሽ በማይልበትና ወደ ወህኒ እየተወረወረ ባለበት ሁኔታ፤*
- *ሕግ አውጪው : (ፓርላማው) አቶ መለስ ሕዝባችንን ሲያንጓጥጡና ሲሳደቡ በሳቅ ለማጀብና የዜጎችን መብት የሚገፍ ሕግ ለማጽደቅ የተሰየመ፤ የወንጀል ተባባሪ በሆነበት፤*
- *ሕግ አስፈጻሚው : ፍርድ ቤትና ዳኞች፤ የፖሊስ ሠራዊቱ፤ ወህኒ ቤቱ የወንጀል ተባባሪ ሆነው፤ የህግ የበላይነት በሌለበት፤*
- *የመገናኛ ብዙሃኑ : ሬዲዮው ቴሌቪዥኑ ጋዜጣው የወያኔ ፕሮፓጋንዳ ብቻ መለፈፊያ በሆኑበት፤ ወቅት*

EthioLion.Com

- ኢኮኖሚው ፡ ባንኩ፤ የንግድ ተቋሙ፤ መሬቱ፤ ወርቅና አልማዙ፤ ቡናው፤ ቪላው (ቤቱ)፤ የጭነት መኪናው አውቶብሶቹ ..........ወዘተ በወያኔ በሞኖፖል ተይዞ፤
- ወያኔ ፡ አሳዳጅ፤ አፋኝ፤ ዘራፊና አዘራፊ፤ ገዳይና፤ አሳሪ በሆነበት ወቅት ሠላሙ የቱ ጋ ነው ያለው ሠላማዊ ትግል የሚሉን ??!!

ሻ'ቢያና ወያኔ እነዚህን የፖለቲካ ተሰፈኞች «በረጅም ገመድ የታሰረች ጥጃ የተለቀቀች ይመስላታል» እያሉ በማሾፍ በልባቸው ሰልጣን ለናንተ ሱሚ ነው ይሏቸዋል ::
እነሱም « የበሬ ሙርጥ ይወድቅልኛል ብላ ስታንጋጥጥ እንደዋለችው » እንሰሳ ማንጋጠጣተውን ቀጥለዋል ::

እኛም ከአይጥ ቤት ጥሬ፤ ከደሮ ወተት፤ ከወያኔ እውነት አይጠበቅምና፤ ይልቅሰ ሕዝባችንን ላገሩና ለመብቱ በአንድላይ እንዲቆም ከሕዝባዊ እምቢተኝነት እስከ አሻፈረኝ በቃ! እንቢ ለመብቴ እንቢ ላገሬ ብሎ በሕብረት እንዲነሳ አድርጉት እንላለን ::

« ግፍና መከራ በደል ሲበዛበት ፤
እንኳንስ የሰው ልጅ ይሸፍታል ወተት ፤ »

በማለት ለአገራችን ለራሳችንና ለልጆቻችን ክብር ሰንል በአንድነት ተባብረን በመነሳት ፡

- የአገራችንን ሃብት እያዘረፍን የተደቀለ ሰንዴ በዕርዳታ መመጽወቱ በቃን እንበል!
- ሻ'ቢያና ወያኔ የጫጉላ ፍቅራቸው ሲደራ በጋራ የኢትዮጵያን ሃብት መዝረፍ፤ አውቀው ሲጣሉ ወገኖቻችን በነሱ የተንኮል ጦርነት መማገዱን በቃ እንበላቸው !
- በዘር፤ በጎሳና በሃይማኖት ተከፋፍለን እርስ በርሳችን አንፋጅም እንቢ እንበላቸው!
- ሕንዶች፤ አረቦችና ቻይናዎች ገበሬው እየተፈናቀለ የተቸበቸበላቸውን መሬት ለአርሶ አደሩ ይመልሱ፤ መሬት ላራሹ እንጂ፤ መሬት ለድንበር ዘለል ከበርቴ አይደለም በቃ እንበላቸው !
- እነዚህ የድንበር ዘለል አጥፊዎች እያደርሱ ያሉትን የደን ሃብታችን ጭፍጨፋና ምንጠራ ይቁም በቃ እንበል !
- እነዚህ የድንበር ዘለል ከበርቴዎች ወደፊት መሬታችንን ለማስጠበቅ በሚል ደባ፤ አገራችንን በቅጥረኛ ወታደሮች አስወርረው ሕዝባችንን ከማስፈጀታቸው በፊት ይህ ወረራ ይቁም በቃ እንበል !
- በእርሻ መሬቱ ላይ በሚጠቀሙት ኬሚካልና፤ የተባይ ማጥፊያ መድሃኒት፤ የአገራችን የከባቢ አየር ከመበከሉ፤ አፈሩ ከመደህየቱ፤ ውሃው ከመመረዙ በፊት በቃ ልንላቸው ይገባል !
- በአዝርዕት ድቀላ የተነሳ፤ የተለያዩ የአገራችን አዝርዕት ተበክለው፤ አገራችን በተፈጥሮ የተለያዩ አዝርዕት የሚበቅልባት መሆኗ ቀርቶ፤ የመከነች አገር ሆና እኛም፤ ቀጣዩም ትውልድ፤ ዘወትር ለማኝ ከመሆናችን በፊት፤ የድቀላ አዝርዕት (በሰው ልጅ ጤናም ላይ የሚያመጣው ጠንቅ ስላለ) በአገራችን አንፈልግም በቃ እንበል !

EthioLion.Com

ይህ ካልሆነ አዛውንቱም ሆነ ወጣቱ፤ ወንዱም ሆነ ሴቱ፤ የተማረም ሆነ ያልተማረ፤ ማንኛችንም እየተፈጸመ ላለው ጥፋት፤ የታሪክ ተጠያቂ ከመሆን አናመልጥም ::

ለመሆኑ አገራችን ኢትዮጵያ ሻ'ቢያን በእንኮኮ ወያኔን በአንቀልባ ተሸክማ እያምላቀቀች ለእኛ ለልጆቿ የእናት እንጀራናት የምትሆነው እስከመቼ ነው ጎበዝ?!

ትናንት የአልባኒያ ሾሻሊዝም አፈ ቀላጤ የነበሩና ዛሬ ደግሞ የምዕራባውያን፤ የአረቦች፤ የሕንዶችና የቻይና አሽከሮች ለሆኑት ወያኔና ሻ'ቢያ በቃ ልንላቸው ይገባል ::

**መደምደሚያ:**

ሕይወት የተንጠለጠለች የውሃ ጠብታ ናት፤ ጥቂት የታደሉ ሰዎች፤ በዚችው በተንጠለጠለች የሕይወት ጠብታ: መሬት ላይ ያለዋጋ ጠብ ብላ ወድቃ እንዳትደርቅ እየሰጉ፤ ታሪክ ሠርተውና በሷ እያጠቀሱ ታሪክ ጽፈው ለራሳቸው፤ ለወገናቸውና ላገራቸው የሚሆን ቁምነገር ሠርተው፤ ለተተኪው ትውልድ ደግሞ ቅርስ ትተው አልፈዋል ::

አብዛኞቻችን እንደ ውሃ የተንጠለጠለችውን የሕይወት ጠብታ፤ ፈራ ተባ እያልን፤ ከዛሬ ነገ፤ ከነገ ለተነገወዲያ፤ ከሳምንቱ ለወር፤ ከዘንድሮ ለከርሞ፤ በማለት በተንጠለጠለችበት ቦታ: በርሃባችን እያከሳናት፤ በፍራቻችን፤ እያስፈራራናት፤ በስንፍናችን እያሳመምናት፤ በዝምታችን እያፈናት፤ በእርዛታችን እያሰበረድናት፤.........ለራሳችንም ሆነ ላገራችን ቁም ነገር ሳንሠራባት ያለዋጋ ከፍራቻችን በሚፈጠረው የሰውነታችን ግለት እንደ እንፋሎት ተና እንድትቀር እናደርጋታለን::

ጥቂቶቻችን ደግሞ በልግመታችን እያበሳጨናት፤ ከጫት ጋር አኝከን እየዋጥናት፤ እያጨስን አጭሰናት፤ በአልኮል ጠብሰናት፤ በወሲብና በዳንኪራ አታክተናት፤ ተማራ ሳትሰናበተን ጠብ ብላ በመውደቅ ከመሬት ጋር ትሳሳማለች::

ከዚያም እከሌ እኮ ሞተ ይባላል! ተኖረና ?!!

ያንተ ወይም ያንቺ ሕይወት እንዴት ናት ወይም ምን ትመስላለች ? ብዬ አልጠይቅም፤ እራሳችሁን ጠይቁ !

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !
ኢትዮጵያ በተባበሩ ልጆቿ ክንድ ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር !!

መጋቢት 10 ቀን 2004 ዓ.ም. (March 21/ 2012)



EthioLion.Com